- የሙሴን ወንድም አሮንን።

- እግዚአብሔር የእርሱ ወንድም አሮን እንደሚረዳው ለሙሴ ቃል ስለገባለት በመጨረሻም ሙሴ ተስማማ።

ዘጸአት 4፥18 & 20

18- ሙሴም ወደ አማቱ ወደ ዮቶር ተመልሶ ሄደና «ወገኖቼ እስከ አሁን በሕይወት መኖራቸውን አይ ዘንድ ወደ ግብፅ ተመልሼ እንድሄድ እባክህ ፍቀድልኝ» አለው። ዮቶርም ሂድ በሰላም ያግባህ» አለው።

20- ስለዚህ ሙሴ ሚስቱንና ልጆቹን በአህያ ላይ አስቀምጦ፣ ወደ ግብፅ አገር መመለስ ጀመረ፤ የእግዚአብሔርንም በትር በእጁ ይዞ ነበር።

- እግዚአብሔር ሙሴን ታገሠው።

- ምንም እንኳን ሙሴ እስራኤላውያንን ለመምራት ባይፈልግም እግዚአብሔር መርጦታል።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባርነት ማውጣት የፈለገው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ ወደዳቸውና በባርነት እንዲኖሩ ስላልፈለገ ነበር።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮቹን ወደ ከነዓን እንደሚመልስ ቃል ገብቶለት ስለ ነበር ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአብርሃም ከዘሮቹ ከእስራኤላውያን አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገብቶ ስለ ነበር ነው።

- በሚቀጥለው ትምህርት እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት እንዳዳነ እንመለከታለን።



ትምህርት 27

1. አዲሱ ንጉስ በእስራኤላውያን ላይ ምን አደረገባቸው?
ሀ- እስራኤላውያንን በሙሉ ባሪያዎች አደረጋቸው።

2. ፈርዖን እስራኤላውያንን ባሪያዎች ያደረጋቸው ለምን ነበር?
ሀ- እስራኤላውያን አገሩን እንዳይወርሱ ስለፈራ ነበር።

3. ፈርዖን እስራኤላውያን አገሩን እንዳይወርሱ የፈራው ለምን ነበር?
ሀ- እስራኤላውያን እጅግ በዝተው ስለነበር ነው።

4. ፈርዖን እስራኤላውያንን ባሪያዎች እንዲያደርጋቸው የመራው ማን ነበር?
ሀ- ሰይጣን።

5. ሰይጣን እስራኤላውያንን ለማጥፋት የፈለገው ለምን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር አዳኝ ከእስራኤላውያን ዘር እንደሚልክ ያውቅ ስለነበር ነው።

6. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የባረካቸው ለምን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለሚወዳቸው ነው።
ለ- እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል የማያጥፍ ስለሆነ ነው።

7. እግዚአብሔር የፈርዖን ሴት ልጅ ሙሴን እንደታሳድገው ለምን አደረገ?
ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሴ መሪነት ከግብፅ ባርነት ለማወጣት ዐቅዶ ስለነበር ነው።

8. እስራኤላውያን ከፈርዖን እጅ ራሳቸውን ማዳን ችለው ነበር?

ሀ- አልቻሉም።

9. ሙሴ እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ ማዳን ችሎ ነበር?

ሀ- አልቻለም።

10. እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ ማዳን የቻለው ማን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

11. ሰዎችን ከሰይጣን እጅ ማዳን የሚችለው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር።

- እስራኤላውያን ለ400 ዓመታት ግብፅ በባርነት ነበሩ።
- እስራኤላውያን እጅግ በጣም ስለ ተሠቃዩ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ።

ዘጸአት 2፡23ለ

23- እስራኤላውያንም በባርነት ከደረሰባቸው ግፍ የተነሣ ይጮኹ ነበር፤ ከባርነት ቀንበር ለመላቀቅ ያሰሙት ጩኸት ወደ እግዚአብሔር ደረሰ።

- እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ጩኸት ሰምቶ ነበር?

ዘጸአት 2፡24-25

24- እግዚአብሔርም የጩኸታቸውን ሲቃ ሰማ፤ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር የገባውንም ቃል ኪዳን አሰበ።



- ሙሴ ለእግዚአብሔር ምን እንዳለው እናንብብ፡

ዘጸአት 4፡13

13- ሙሴ ግን «ጌታ ሆይ፣ እባክህ ሌላ ሰው ላክ» አለው።

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ ለመምራት ስለፈራ እግዚአብሔር ሙሴን ተቆጣው።

- ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴ ለፈርዖን ሲናገር ከእርሱ ጋር በመሆን የሚረዳውን ሌላ ሰው እንደሚልክ ቃል ገባለት።

ዘጸአት 4፡14-17

14- በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ፤ «ሌዋዊው ወንድምህ አሮን አለ አይደል? እርሱ ጥሩ እንደሚናገር አውቃለሁ፤ እንዲያውም አሁን ወደ አንተ እየመጣ ነው፤ በሚያይህም ጊዜ ከልቡ ደስ ይለዋል።

15- ለእርሱም ትነግረዋለህ፤ የሚናገራቸውንም ቃላት በአንደበቱ ታኖራለህ፤ ሁለታችሁም በትክክል እንድትናገሩ እረዳችኋለሁ፤ ምን ማድረግ እንዳለባችሁም አስተምራችኋለሁ።

16- አንተ እንደ አምላኩ ሆነህ ትነግረዋለህ፤ እርሱም እንደ አንደበትህ ሆኖ ለሕዝቡ ይናገርልሃል።

17- ተአምራዊ ምልክት እንድታሳዩበት ይህችን በትር በእጅህ ይዘህ ሂድ።»

- እግዚአብሔር ሙሴ ወደ ፈርዖን ሲሄድ እንዲረዳው የላከው ማንን ነበር?

10- ሙሴም እግዚአብሔርን፣ «ጌታ ሆይ፤ ቀድሞም ሆነ፣ አንተ ከባሪያህ ጋር ከተነጋገርህ ወዲህ፣ ከቶ አንደበተ ርቱዕ ሰው አይደለሁም። እኔ ኮልታፋና ንግግር የማልችል ሰው ነኝ» አለው።

- ሙሴ እግዚአብሔርን በደንብ መናገር አልችልም አለው።

- እግዚአብሔር ምን መለሰለት?

ዘጸአት 4፥11-12

11- እግዚአብሔርም ሙሴን፣ «ለሰው አንደበቱን የሰጠው ማን ነው? ሰውን ደንቆሮ ወይም ዲዳ የሚያደርገው ማን ነው? ዓይን የሚሰጥ ወይም ዕውር የሚያደርገውስ ማን ነው?

12- እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? በል አሁን ሂድ እኔ እንድትናገር አደርግሃለሁ፤ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ» አለው።

- ለሙሴ የንግግር ችሎታ የሰጠው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- ሙሴ በሚገባ መናገር እንዲችል መርዳት የሚችለው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር ሙሴ በሚገባ መናገር እንዲችል እንደሚረዳው ነግሮት ነበር።

- እግዚአብሔር ሙሴን ሊረዳው ቢፈልግም አሁንም ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ መምራት አልፈለገም።



25- እግዚአብሔርም እስራኤላውያንን ተመለከተ፤ ስለ እነርሱም ገደደው።

- እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ጩኸት ሰምቷል።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል አሰበ።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባው ቃል ምን ነበር?

- እግዚአብሔር የገባው ቃል ከ400 ዓመታት በኋላ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን ምድር መመልስ ነው።

- ምናልባት እስራኤላውያን እግዚአብሔር እንደረሳቸው አስበው ይሆናል እግዚአብሔር ግን አልረሳቸውም።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ቃል የገባውን ነገር ያደርገዋል።

- እግዚአብሔር ባይጣደፍም ቃል የገባውን ነገር ሁልጊዜ በራሱ ጊዜ ይፈጽመዋል።

- በዚያን ጊዜ ሙሴ የት ነበር ያለው?

- እግዚአብሔር በሙሴ መርነት እስራኤላውያንን ከግብፅ ለማውጣት አላቀደም ነበር?

- እግዚአብሔር በሙሴ መርነት እስራኤላውያንን ከባርነትለማውጣት አላቀደም ነበር?

- ፈርዖን ሊገድለው ስለ ፈለገ ሙሴ ወደ ምድያም ምድር ኮብልሏል።

- በምድያም ምድር ሆኖ ሙሴ ሚስት አግብቶ ሁለት ወንዶች ልጆችንም ወለዷል።

- አንድ ቀን ሙሴ የአማቱን በጐች በመጠበቅ ላይ ሳለ እንግዳ ነገር ተመለከተ።

ዘጸአት 3፡1-3

1- አንድ ቀን ሙሴ የምድያም ካህን የሆነውን የዮቶር በጎችና ፍየሎች እየጠበቀ ሳለ፣ መንጋውን እየነዳ ወደ ምድረ በዳው ዳርቻ አምርቶ የእግዚአብሔር ተራራ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ኮሬብ ቀረበ።

2- እዚያም የእግዚአብሔር መልአክ በቁጥቋጦው ውስጥ በሚንቀለቀል የእሳት ነበልባል መካከል ተገለጠለት። ሙሴም ቁጥቋጦው በእሳት ቢያያዝም እንኳ፣ አለመቃጠሉን አየ።

3- ሙሴም «ቁጥቋጦው ለምን እንደማይቃጠል ቀረብ ብዬ ይህን አስገራሚ ነገር ልመልከት» አለ።

- ሙሴ ምን አየ?

- ሙሴ ቁጥቋጦ ላይ እሳት እየነደደ ነገር ግን ቁጥቋጦ አለመቃጠሉን አየ።

- ሙሴ ሲነድድ ያየው ቁጥቋጦ ያልተቃጠለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም በቁጥቋጦው ውስጥ እግዚአብሔር ስለነበረ ነው።

- እግዚአብሔር በቁጥቋጦው ውስጥ ስለ ነበረ ቁጥቋጦው አልተቃጠለም።



7- «አሁንም ደግሞ እጅህን ወደ ብብትህ መልሰህ አስገባ» አለው። ሙሴም እጁን መልሶ ብብቱ ውስጥ አስገባ፤ እንደገና እጁን ከብብቱ ውስጥ ባወጣት ጊዜ፣ ተመልሳ እንደሌላው የሰውነቱ ክፍል ሆነች።

8- እግዚአብሔርም «እንግዲህ ባያምኑህ ወይም የመጀመሪያውን ተአምራዊ ምልክት ባይቀበሉ እንኳ፣ ሁለተኛውን ያምናሉ።

9- እነዚህን ሁለት ምልክቶች ባያምኑ ወይም ቃልህን ባይቀበሉ ግን፣ ከዐባይ ወንዝ ጥቂት ውኃ ቀድተህ በደረቅ ምድር ላይ አፍስሰው። ከወንዙም ቀድተህ ያፈሰስኸው ውኃ በምድር ላይ ደም ይሆናል።»

- እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር አውጥቶ እንዲመራ የመረጠው መሆኑን የሚያሳየው የመጀመሪያ ምልክት ምን ነበር?

- የሙሴ በትር ወደ እባብነት መለወጥ እና ተመልሳ በትር መሆን።

- እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ እንዲያወጣቸው፥ መምረጡን የሚያሳየው ሁለተኛው ምልክት ምን ነበር?

- ሙሴ እጁን በብብቱ ውስጥ አስገብቶ ሲያወጣው እጁ ለምፃም መሆኑና፤ መልሶም በብብቱ ውስጥ ሲያስገባው እጁ ጤናማ መሆኑ ነው።

- ከእግዚአብሔር ዘንድ ሁለቱ ምልክቶች ቢሰጡትም እስራኤላውያን ላይከተሉኝ ይችላሉ በማለት ሙሴ አሁንም ፈራ።

- ሙሴ ለእግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይህ ነው፡

ዘጸአት 4፡10

- ሙሴ እስራኤላውያንን መርቶ ከግብፅ ያወጣ ዘንድ እግዚአብሔር እርሱን እንደ መረጠው እስራኤላውያን አያምኑም ብሎ ፈራ።

- ሙሴ ለእግዚአብሔር የተናገረው ይህን ነበር፡

ዘጸአት 4፡1

1- ሙሴም «ባያምኑብኝስ፤ ቃሌን ባይቀበሉስ፤ “እግዚአብሔር አልተገለጠልህም” ቢሉኝስ?» ብሎ መለሰ።

- ሙሴ ስለ ፈራ እግዚአብሔር ሙሴ ሁለት ምልክቶችን ለእስራኤላውያን እንዲያሳይ ሰጠው።

ዘጸአት 4፡2-9

2- እግዚአብሔር፣ «በእጅህ የያዝሃት እርሷ ምንድን ናት?» ሲል ጠየቀው፤ እርሱም መለሰ፣ «በትር ናት» አለው።

3- እግዚአብሔርም፣ «መሬት ላይ ጣላት» አለው። ሙሴ በትሩን መሬት ላይ ጣላት፤ እባብም ሆነች፤ ከአጠገቧም ሸሸ።

4- እግዚአብሔር ሙሴን፣ «በል እጅህን ዘርጋና ጅራቷን ያዛት» አለው። ሙሴም እጁን ዘርግቶ ሲይዛት፣ እባቧ ተለውጣ በእጁ ላይ እንደገና በትር ሆነች።

5- እግዚአብሔርም «ይህ የሆነው፥ የአባቶቻቸው አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር የተገለጠልህ መሆኑን እንዲያምኑ ነው» አለው።

6- እግዚአብሔርም ደግሞ፣ «እጅህን ብብትህ ውስጥ አስገባ» አለው። ሙሴም እጁን ብብቱ ውስጥ አስገባ፤ ከብብቱም ውስጥ ባወጣት ጊዜ እጁ እንደ በረዶ ለምጽ ሆነች።



- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

- እግዚአብሔር የሚያደርገውን ማንም ማድረግ አይችልም።

- እግዚአብሔር በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ የነበረው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ቁጥቋጦ ውስጥ የነበረው ስለ እስራኤላውያን ከሙሴ ጋር ለመነጋገር ፈልጎ ነው።

- የሚቃጠለው ቁጥቋጦ ከእስራኤላውያን ጋር የሚመሳሰለው በምንድን ነው?

- እሳቱ ቁጥቋጦውን ሊያጠፋ እንደ ፈለገ ሁሉ ሰይጣንና ፈርዖንም እስራኤላውያንን ለማጥፋት በመፈልጋቸው ነው።

- እግዚአብሔር በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ እንደ ነበረ ሁሉ ከእስራኤላውያንም ጋር በመሆኑ ነው።

- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር በመኖሩ፥ሰይጣንና ፈርዖን ሊያጠፏቸው አልቻሉም ነበር።

- ከቁጥቋጦው ውስጥ እግዚአብሔር የሙሴን ስም ጠራ።

ዘጸአት 3፡4

4- ሙሴ ሁኔታውን ለመመልከት መቅረቡን እግዚአብሔር ባየ ጊዜ፣ ከቁጥቋጦው ውስጥ እግዚአብሔር፣ «ሙሴ፣ ሙሴ፣» ብሎ ጠራው። ሙሴም፣ «አቤት እነሆኝ» አለው።

- ሙሴ እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እስኪጠራው ድረስ እግዚአብሔር በቁጥቋጦው ውስጥ መኖሩን አላወቀም ነበር።

- እግዚአብሔር የሙሴን ቋንቋ እንዴት አወቀ?

- እግዚአብሔር ሁሉንም ቋንቋዎች ያውቃል።
- እግዚአብሔር የማያውቀው አንድም ቋንቋ የለም።

- እግዚአብሔር የእናንተንም ቋንቋ ያውቃል።

- እግዚአብሔር የምትናገሩትን ሁሉ ይሰማል።
- እግዚአብሔር የምትናገሩትን ሁሉ ይረዳል።

- በሹክሹክታ ብትናገሩ እንኳ እግዚአብሔር ይሰማል።

- እግዚአብሔር ከሚነድደው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ለሙሴ እንደገና ተናገረ፡

ዘጸአት 3፡5-6

5- እግዚአብሔርም፣ «ወደዚህ እንዳትቀርብ፤ ይህች የቆምህባት ምድር የተቀደሰች ስለ ሆነች ጫማህን አውልቅ» አለው።

6- ቀጥሎም፣ «እኔ የአባቶችህ አምላክ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፥ የያዕቆብ አምላክ ነኝ» አለው። በዚህ ጊዜ ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ማየት ስለ ፈራ፣ ፊቱን ሸፈነ።

- እግዚአብሔር ሙሴ ጫማዎቹን እንዲያወልቅ የነገረው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሙሴ የቆመው በፍጹም አምላክ ፊት ስለነበር ነው።



- ፈርዖን እስራኤላውያን ግብፅን ለቅቀው እንዲሄዱ ይፈቅድ ይሁን?

- እግዚአብሔር ያለው እንዲህ ነው፡

ዘጸአት 3፡19-20

19- እግዚአብሔርም ደግሞ እንዲህ አለ፥ «የግብፅ ንጉሥ ግን በኃያል ክንድ ካልተገደደ በስተቀር መቼም እንደማይለቃችሁ አውቃለሁ።

20- ስለዚህ እኔ እጅግ ድንቅ የሆኑ ተአምራትን እዚያው እመካከላቸው በማድረግ ክንዴን ዘርግቼ ግብፃውያንን እመታቸዋለሁ፤ ከዚያም በኋላ፣ እንድትሄዱ ይለቃችኋል።»

- እስራኤላውያንን ግብፅን ለቅቀው እንዲሄዱ ፈርዖን እንደማይፈቅድ እግዚአብሔር ያውቃል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ፈርዖን እስራኤላውያንን ግብፅን ለቅቀው እንዲሄዱ እንደማይፈቅድ በምን አወቀ?

- እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል።

- ከማሰባችሁ በፊት አሳባችሁን እግዚአብሔር ያውቃል።

- ከመናገራችሁ በፊት ቃላችሁን እግዚአብሔር ያውቃል።

- አንድ ነገር ከማድረጋችሁ በፊት ምን ልታደርጉ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ያውቃል።

- እግዚአብሔር መጀመሪያ የለውም ማለት ነው።

- እግዚአብሔር መጨረሻ የለውም ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜም አለ ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ፈጽሞ የለም ማለት ነው።

- እግዚአብሔርም ደግሞ ለሙሴ እንዲህ አለው፡-

ዘጸአት 3፡15-18ሀ

15- ደግሞም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «የአባታችሁ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ወደ እናንተ ልኮኛል፤ ስሜም ለዘለዓለም ይኸው ነው። ወደፊት በተከታታይ በሚነሣው ትውልድ ሁሉ የምታስበው በዚህ ስም ነው ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው» አለው።

16- «ሂድና የእስራኤልን አለቆች ሰብስበህ፣ የአባቶቻችሁ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ተገለጠልኝና እንዲህ አለኝ፤ ጐብኝቻችኋለሁ፤ በግብፅ የደረሰባችሁንም አይቻለሁ።

17- ስለዚህም በግብፅ ከምትቀበሉት መከራ አውጥቼ ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደ ከነዓናውያን፣ ወደ ኬጢያውያን፣ ወደ አሞራውያን፣ ወደ ፌርዛውያን፥ ወደ ኤውያውያንና ኢያቡሳውያን ምድር አገባችኋላሁ ብሎአል ብለህ ንገራቸው» አለኝ።

18- የእስራኤል አለቆችም ይሰሙሃል።»

- እግዚአብሔርም ሙሴን ለእስራኤላውያን የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ከባርነት እንዳወጣችሁ ላከኝ ብለህ ንገራቸው አለው።



- ምክንያቱም ሙሴ የቆመው በቅዱስ አምላክ ፊት ስለነበር ነው።

- እግዚአብሔር ስለ እስራኤላውያን ለሙሴ ነገረው።

ዘጸአት 3፡7-10

7- ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ «በግብፅ አገር የሚኖሩትን የሕዝቤን መከራ አይቼአለሁ፤ ከአሠሪዎቻቸው ጭካኔ የተነሣ የሚያሰሙትንም ጩኸት ሰምቻለሁ፤ሥቃያቸውንም ተረድቼአለሁ።

8- ስለዚህም ከግብፃውያን እጅ ልታደጋቸውና ማርና ወተት ወደምታፈሰው ሰፊና ለም ወደ ሆነችው. . . ምድር ላወጣቸው ወርጃለሁ።

9- አሁንም የእስራኤል ልጆች ጩኸት ወደ እኔ ደርሶአል፤ ግብፃውያን የሚያደርሱባቸውን ግፍ አይቻለሁ።

10- በል እንግዲህ ና፤ ሕዝቤን፥ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ምድር እንድታወጣቸው ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ።»

- እግዚአብሔር ለሙሴ የእስራኤላውያንን ጩኸት መስማቱን ነገረው።

- እግዚአብሔር ለሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት መርቶ እንዲያስወጣቸው እርሱን መምረጡን ነገረው።

- እግዚአብሔር ለሙሴ እስራኤላውያንን መርቶ ወደ ከነዓን ምድር እንዲመልሳቸው እርሱን መምረጡን ነገረው።

- ሙሴ ለእግዚአብሔር የሰጠው መልስ ምን ነበር?

ዘፍጥረት 3፡11

11- ሙሴ እግዚአብሔርን፣ «ወደ ፈርዖን የምሄድና የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ?» አለው።

- ሙሴ ለእግዚአብሔር «እኔ እስራኤላውያንን ከግብፅ ማውጣት አልችልም» አለው።

- ሙሴ ለእግዚአብሔር «እኔ እስራኤላውያንን ከግብፅ ማውጣት አልችልም» ያለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ሙሴ እስራኤላዊውን ሊረዳ ሞክሮ ያልተሳካለትን ጊዜ ስላስታወሰ ነው።

- እግዚአብሔር ለሙሴ ምን ብሎ መለሰለት?

ዘጸአት 3፡12

12- እግዚአብሔር፣ «እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ እኔ የላክሁህ ለመሆኑ ምልክቱ ይህ ነው ሕዝቡን ከግብፅ ካወጣሃቸው በኋላ፣ በዚህ ተራራ ላይ እግዚአብሔርን ታመልካላችሁ» አለው።

- እግዚአብሔር ለሙሴ አብሬህ እሆናለሁ አለው።
- እግዚአብሔር ለሙሴ ምልክትን ሰጠው።

- እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ምልክት ምን ነበር?

- እግዚአብሔር ሙሴን ቆሞ ወደ ነበረበት፥ የሚቃጠለው ቁጥቋጦ ወዳለበት ተራራ መልሶ የሚያመጣው መሆኑን ቃል መግባቱ ነበር።



- የተራራው ስም የሲና ተራራ ነበር።
- ሙሴ ለእግዚአብሔር ምን አለው?

ዘጸአት 3፡13

13- ሙሴም እግዚአብሔርን፣ «ወደ እስራኤል ልጆች ሄጄ፣ "የአባቶቻችሁ አምላክ፣ ወደ እናንተ ልኮኛል" ስላቸው "ስሙ ማን ነው?" ብለው ቢጠይቁኝ ምን እላቸዋለሁ?» አለው።

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከባርነት እንዳወጣቸው የላከኝ እግዚአብሔር መሆኑን ስነግራቸው አያምኑኝም ብሎ ፈራ።

- ስለዚህ ሙሴ ለእስራኤላውያን እንዲነግራቸው የእግዚአብሔርን ስም ጠየቀ።

- እግዚአብሔር ምን ብሎ መለሰለት?

ዘጸአት 3፡14

14- እግዚአብሔርም ሙሴን «እኔ ያለሁና የምኖር ነኝ፤ ስለዚህም "ያለና የሚኖር ልኮኛል" ብለህ ነገራቸው።»

- እግዚአብሔር ሙሴን «ያለና የሚኖር» እስራኤላውያንን ከባርነት ነፃ እንዳወጣቸው ላከኝ ብለህ ንገራቸው አለው።

- «ያለና የሚኖር » የሚለው የእግዚአብሔር ስም ትርጉሙ ምንድን ነው?